የሰ/መ. ቁ. 22038

16/10/1998 ዓ/ም

ዳኞች 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. ” ተገኔ ጌታነህ

4. ” መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ

ተጠሪ፡-እነ አቶ ግርማ ታከለ /8 ሠዎች/

# ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የጀመረው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ላይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በቦርዱ ባቀረቡት ክስ አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ደረጃ ያለአግባብ ከደረጃ 4 ወደ ደረጃ 3 ዝቅ ከማድረጉም ሌላ ደረጃ 4 የነበሩትን የሥራ ባልደረቦቻቸውን ወደ ደረጃ 5 ያሣደጋቸው በመሆኑ ወደ ደረጃ 5 የሥራ ደረጃ እንዲያድጉ እንዲወሠንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ቦርዱም ተጠሪዎች በተላላኪነት የሥራ መደብ ላይ ሆነው ፍፁም በተለየው ለጥበቃ የሥራ መደብ የተሠጠው ደረጃ ይሠጠን ያሉ በመሆኑና ይህ የሚፈፀመው ደግሞ በውድድር እንጂ በጥያቄ ብቻ ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ተጠሪዎች በጥበቃ የሥራ መደብ ያገኙት ደረጃ 4 ወደ ተላላኪነት ሲመደቡ ይህ ደረጃ የተለወጠበትን የህግ አግባብ ሣያስረዳ ከደረጃቸው ዝቅ ሊያደርጋቸው ስለማይችልና በአዲሱ የስራ መደብና የደሞዝ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን 26/11/98

ማያስረዳ ከደረጃቸው ዝቅ ሊያደርጋቸው ስለማይችልና በአዲሱ የስራ መደብና የደሞዝ እስኬል ደግሞ የቀድሞ የጥበቃ ሥራ መደብ ደረጃ 4 ወደ ደረጃ ከፍ በመደረጉ ተጠሪዎች የጠየቁት ደረጃ 5 እንዲሠጣቸው ወስኗል።

የአሁኑ የሠበር አቤቱት የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው ይህ ችሎትም ለተጠሪዎች የጠየቁት ደረጃ 5 እንዲሠጣቸው የተሠጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩን ለሠበር አስቀርቧል። ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፁሁፍ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል።

ከግራ ቀኙ ክርክርና ከመዝገቡ ተጠሪዎች ቀደም ሲል በጥበቃ ሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተሠጣቸው ደረጃ 4 ወደ ተላላኪነት የሥራ መደብ ሲዛወሩ ወደ ደረጃ 3 ዝቅ መደረጉን በዚህም ምክንያት ክስ አቅርበው ደረጃቸው ወደ ደረጃ 4 እንዲስተካከል በመወሠኑ በዚሁ መሠረት ማስተካከሉን አዲሱ የሥራ ደረጃና የደመወዝ እስኬል ሲወጣም ተጠሪዎች እየሠሩበት ያለው የተላላኪነት የሥራ መደብ ደረጃ 3 በመሆኑ የተጠሪዎችም የሥራ ደረጃ በዚሁ መሠረት መስተካከሉን ተረድተናል። በመሆኑም የተጠሪዎች የሥራ መደብ ከደረጃ 4 ወደ ደረጃ 3 ዝቅ የመደረጉን አግባብነት እንዲሁም ተጠሪዎች እንደሚጠይቁት ደረጃቸው ወደ ደረጃ 5 ከፍ ሊደርግ የሚገባ መሆን አለመሆኑን ችሎቱ ተመልክቷል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች መ/ቤት ተጠሪዎች ከጥበቃ የሥራ መደብ ወደ ተላላኪት ሲዛወሩ ሲዛወር ለተላላኪ የሥራ መደብ የተሰጠውን ደረጃ 3 እንዲሠጣቸው በማድረጉ በቀረበበት ክስ የተጠሪዎችን የሥራ ደረጃ ቀድሞ ወደ ነበረበት ደረጃ 4 መልሷል። በመሆኑም ተጠሪዎች ለዚህ የሥራ ደረጃ የሚሠጠውን ጥቅም የማግኘት መብታቸው በውሣኔው ተረጋግጧል። ከዚህ የሥራ ደረጃና የደመወዝ ስኬል ዝቅ ሊደረጉና መብታቸውን ሊያጡ የሚገባውም ህጋዊ ምክንያት ሲያጋጥም ብቻ ነው።

ፍርድ ቤት
ፊርማ ... ቀን 26/11/98

ቀድሞ በነበረው የሥራ ደረጃና የደመወዝ ስኬል መሠረት ለደረጃ 4 የተሠጠው የደመወዝ መነሻ ብር 419 ሲሆን መድረሻው ደግሞ ብር 839 ነው። አመልካች ግን የተጠሪዎችን የሥራ ደረጃ ወደ ደረጃ 3 ዝቅ ያደረገው ሲሆን ለዚህም የሠጠው ምክንያት መ/ቤቱ በተደረገው ጥናት አዲስ የደረጃና የደመወዝ ስኬል ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በዚህ ስኬል መሠረት ለተላላኪነት የሥራ መደብ የተሠጠው ደረጃ 3 በመሆኑና ተጠሪዎችም የሚሠሩት በዚሁ የስራ መደብ ስለሆነ የሥራ ደረጃቸው በዚሁ መሠረት እንዲስተካከል የተደረገ ሲሆን በተደረገው ለውጥም የተጠሪዎች ደመወዝ አልተነካባቸውም የሚል ነው ።ይሁን እንጂ ምንም እንኳን የደረጃ ለውጡ ተጠሪዎች አሁን እያገኙ ባሉን የደመወዝ መጠን ላይ ያመጣው ለውጥ ባይኖርም ወደፊት ሊደርሱበት የሚችሉት የደመወዝ ጣሪያ ላይ ግን አሉታዊ ውጤት ማስከተሉ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም በአዲሱ ስኬል መሠረት የደረጃ 3 መነሻ ደመወዝ ብር 382 ሲሆን መድረሻው ደግሞ ብር 818 ነው። በቀድሞ ስኬል ደረጃ 4 ያገኙ የነበረው የመነሻና የመድረሻ ደመወዝ ስኬል በአዲሱ ስኬል ለደረጃ 3 ከተሠጠው የመነሻና የመድረሻ ስኬል በብልጫ ልዩነት ያለው በመሆኑም ተጠሪዎች ያለህጋዊ ምክንያት መብታቸውን ሊያጡ አይገባም።

በሌላ በኩል ግን ተጠሪዎች አሁን እየሠራበት ያለው የሥራ መደብ የተላላኪነት የሥራ መደብ በመሆኑ ሊጠይቁ የሚችሉት ለዚሁ የሥራ መደብ የተሰጠውን ጥቅም እንጂ ቀድሞ ሲሠራበት በነበረው የጥበቃ የሥራ መደብ የተሰጠውን አይደለም። ስለሆነም በአዲሱ ስኬል ለጥበቃ የሥራ መደብ የተሠጠው ደረጃ 5 እንዲሠጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት የለውም።

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በተዘረዘሩት ምክንያቶችና ተጠሪዎች ለጥበቃ የሥራ መደብ የተሰጠው የሥራ ደረጃ እንዲሠጣቸው መወሰኑ ስህተት መሆኑን ተረድተናል።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን

# ውሣኔ

1) የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ.160/02/97 በ8/6/97 የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2) የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 37570 በ29/02/98 የሠጠው ውሣኔ ተሻሽሎል፡፡

3) ተጠሪዎች በአዲሱ የሥራ መደብና የደመወዝ እስኬል የተቀመጠው ደረጃ 4 የሥራ ደረጃ ይሠጣቸው

4) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ቃ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፊርማ [signature] ቀን 28/11/95

-1-